BACK

SPINE

FRONT

# ይቅርታን ማድረግ

በእነዚህ አራት ተከታታይ ትምህርቶች ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ፍቅር፣ ይቅርታን ስለማድረግ፣ ስለ እውነተኛ ይቅርታ ምልክቶች እና ስለ እርቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች ተሰጥተዋል። በእርግጥ ይቅርታን ማድረጌን በምን አውቃለው? ይቅርታን አድርጌ አለመታረቅ ይቻላል ወይ? ምሬት ምን ማለት ነው? ተበድዬም ይቅርታን መጠየቅ አለብኝ ወይ? በእነዚህ ሲዲዎች ላይ ያለው ትምህርት እነዚህንና የመሳሰሉት ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል። ምሬት እንደ እሳት ፍም እጃችን ላይ ያቆየነው ያህል ያቃጥለናል። ይቅርታን አለማድረግ ደግሞ መርዙን እየጠጣን ጉዳት ያደረሰብን ሰው እንዲሞት መጠባበቅ ማለት ነው ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን መቀበል የሚበድሉንን የመማር ኃላፊነት መቀበል ማለት ነው። ምክንያቱም ወንጌላችን የምህረትና የእርቅ አዋጅ ነው። በበደልነው እግዚአብሔር ተለቀን የበደሉንን ማነቅ አይቻልም። ምንም እንኳ ይህን የሚያደርጉ ክርስቲያኖች ቢኖሩም ከወንጌል እውነት ጋር የሚጻረር በግዜም በዘላለምም አላስፈላጊ ዋጋ የሚያስከፍል የኪሳራ ልምምድ ነው። ለአንድ ክርስቲያን መማር እግዚአብሔርን መምሰሉን ከሚያሳይበት መንገዶች አንዱ ነው። ወንጌል በዳይ እንዲለወጥ ተበዳይ ደግሞ እንዲምር ብሎም በዳይ ሲለወጥ ተበዳይ ደግሞ ሲምር እንዲታረቁ ያዛል። ይህ ትእዛዝ ግን የተሰጠው እንደገና በክርስቶስ ለተፈጠረው አዲሱ ሰው ነው። በጥልቅና በሰፊው እነዚህን እውነቶች ለመረዳት ሲዲውን በማስተዋል እንዲሰሙ ከሰሙም በኃላ ላልሰሙት ይህን የይቅርታንና የእርቅ መልእክት እንዲያስተላልፉ ለአድማጮቻችን ሁሉ እንጠይቃለን።



“እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ” ኤፌሶን 4:32
“ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን … እወድዳለሁና” ሆሴዕ 6:6

ይህ መልዕክት ለእርስዎና ለቤተሰብዎ እንዲሁም ለሚያውቋቸው ሁሉ ታላቅ የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚያመጣ ስለሆነ ረጋ ብለው ቢያዳምጡትና ደጋግመው ቢሰሙት እንደሚጠቀሙበት የጌታም መንፈስ የቃሉን ፍቺ እንደሚያበራልዎ በመተማመን ምንም ዓይነት ጥያቄና አስተያየት ቢኖርዎት በስልክ ወይንም በአድራሻችን ቢጽፉልን ይደርሰናል::

ሜኔሶታ በምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ምክትል መጋቢ
መጋቢ እስጢፋኖስ አለሙ 2011

Ethiopian Evangelical Church In Minnesota ◆ 770 7th st. East ◆ St.Paul, MN 55106
(651) 772 0216 ◆ www.eecmn.org

ዋጋ 10.00

ይቅርታን ማድረግ በፓስተር እስጢፋኖስ አለሙ 4 CDS

